# ጥሬ ገንዘብ፣ወርቅ እና የውጭ ሀገር ገንዘብ የመያዝና የማዘዋወር፣ ገንዘብ የማስተላለፍ የሀዋላ ስራ እንዲሁም ሀሰተኛ የገንዘብ ኖት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ሕገ ወጥ ድርጊት መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና የወሮታ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 931/2015

Directive on the Handling, Transfer, and Exchange of Foreign Currency, Gold, and Cash, Including Information on Illegal Currency Transactions and Counterfeit Banknotes, as well as the Procedures for Prosecution and Penalties (Directive No. 931/2015)

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
National Bank of Ethiopia

መስከረም 26፥ 2015

# ጥሬ ገንዘብ ፤ወርቅ እና የዉጭ ሀገር ገንዘብ የመያዝና የማዘዋወር ፣ ገንዘብ የማስተላለፍ ሀዋላ ስራ እንዲሁም ሀሰተኛ የገንዝብ ኖት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ሕገ ወጥ ድርጊት መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና የወሮታ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 931/2015

የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ገንዘቦችን እንዲሁም ወርቅን ከተፈቀደው መጠን በላይ ህገወጥ በሆነ እና ባልተገባ መልኩ ይዞ የመገኘት እና የማዘዋወር ስጋት እንዲሁም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ፣

ወርቅ፤ህገወጥ ገንዘብ፡ እንዲሁም ሀሰተኛ የገንዝብ ኖት ይዞ ከመገኘት እና ከማዘዋወር ጋር በተያያዘ እንዲሁም ህገወጥ በሆነ መንገድ ያለፈቃድ ገንዘብ የማስተላለፍ የሀዋላ ስራ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተገቢው መንገድ እና በመረጃ በመታገዝ መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ እና ለዚህም አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ጠቋሚዎች እና ያገኙ ከተግባራቸው ጋር የተመጣጠነ የማበረታቻ ወሮታ ሊከፈላቸው የሚገባ በመሆኑ፣

የኢትዮጵየ ብሔራዊ ባንክ በየኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ /እንደተሻሻለ/አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 21(5(ለ) እና አንቀጽ 27(2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

*ይህ መመሪያ* ***"ጥሬ ገንዘብ፤ ወርቅ እና የዉጭ ሀገር ገንዘብ የመያዝና የማዘዋወር ፣ ገንዘብ የማስተላለፍ የሀዋላ ስራ እንዲሁም ሀሰተኛ የገንዝብ ኖትጋር በተያያዘ የሚፈጸም ሕገ ወጥ ድርጊት መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና የወሮታ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር*** 931/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

*ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፡-*

1. **"የውጭ አገር ገንዘብ"** *ማለት ከኢትዮጵያ ገንዘብ በስተቀር ከኢትዮጵያ ውጭ በማናቸዉም ሃገር ሕጋዊ ገንዘብ የሆነና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረግ ክፍያ ተቀባይነት እንዳለው ብሔራዊ ባንክ ያሳወቀው ማናቸዉም ገንዘብ ነው፡፡*
2. **"ሕገ ወጥ ዕቃ"** *ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ /እንደተሻሻለ/አዋጅ ቁጥር* 591/2000 *ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ በግለሰብ ወይም በድርጅት የተከማቸ ወይም የሚዘዋወር ጥሬ ብር ወይም ወርቅ ወይም የዉጭ ሀገር ገንዘብ ወይም ሀሰተኛ የገንዘብ ኖት ነው፡፡*
3. **"ጥቆማ"** *ማለት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ለሕግ አስከባሪ አካል ስለ ሕገ-ወጥ ድርጊት የሚቀርብ መረጃ ነው፡፡*
4. **"ጠቋሚ"** *ማለት ስለ ሕገ-ወጥ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ወይም ህገ ወጥ ድርጊቶች የተመለከተ መረጃ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ለሕግ አስከባሪ አካል የሚሰጥ ሰዉ ነዉ፡፡*
5. **"ሠራተኛ"** *ማለት በብሔራዊ ባንክ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሠራተኛ ነው፡፡*
6. **"የወሮታ ክፍያ"** *ማለት በጥቆማ ሕገ-ወጥ ዕቃ ተይዞና በሕግ ተወርሶ ለባንኩ ገቢ ሲሆን ዕቃዉን ለያዙ ወይም ዕቃዉ እንዲያዝ ጥቆማ ለሰጡ ወይም ህገ ወጥ ድርጊትን የፈጸሙ አካላትን በመጠቆም ተጠያቂነት እንዲሰፍን ላደረጉ ሰዎች የሚሰጥ ክፍያ ነው፡፡*

7. **"ህገ ወጥ ገንዘብ ማስተላላፍ ሀዋላ ስራ"** ማለት ከብሄራዊ ባንክ ፈቃድ ካገኙ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ተቋማቱን ወኪል በማድረግ የገንዘብ ማስተላለፍ ስራ ከሚሰሩ ህጋዊ የገንዘብ አስተላለፊ ድርጅቶች ውጭ ባሉ ህገ ወጥ አካላት በተለይም የፋይናንስ ተቋማቱን አውታር እና ሲስተም ለዚህ አላማ በመጠቀም ገንዘብ ከአንድ አካል ወደ ሌላ የማስተላለፍ ስራ ነው፡፡
8. **"ሕግ አስከባሪ ወይም ያዥ"** ማለት በሕግ ማስከበር ተግባር ላይ የተሰማራ የፌዴራል ወይም የክልል መንግስት አካል የሆነ የታጠቀ ወይም ያልታጠቀ ኃይል ወይም የሀገር መከላከያ ሠራዊት ነው፡፡
9. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር 591/2000 ነዉ፡፡
10. **"ብሔራዊ ባንክ "** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነዉ፡፡
11. **"መረጃ"** ማለት በሕግ ከተፈቀደዉ መጠን በላይ ጥሬ ብር ፣ ወርቅ ወይም የዉጭ ሀገር ገንዘብ የያዘን ሰዉ ወይም ሕገ ወጥ የዉጭ ሀገር ገንዘብ ዝውውር ወይም መያዝን፣ ሀሰተኛ የገንዝብ ኖት መያዝን ወይም ማዘዋወርን፣ የሀሰተኛ የገንዘብ ኖት የሚያትሙ አካላትን እና የሚያትሙባቸው ቦታዎች እና መሳሪያዎችን ወይም ህገወጥ በሆነ ገንዘብ የማስተላለፍ ሀዋላ ድርጊትን በተመለከተ የሚቀርብ ብሔራዊ ባንክ ወይም የሕግ አስከባሪ አካል ሊደርስበት የማይችል መረጃ ነው፡፡
12. **"ተጨባጭ መረጃ"** ማለት የቀረበው መረጃ አግባብነት ባለዉ አካል ተጣርቶ ከተገኘው ውጤት ጋር ሲመሳከር ግኝቱና መረጃው አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ወይም እውነት ሆኖ የተገኘ መረጃ ነው፡፡
13. **"ማስረጃ"** ማለት የጽሁፍ እና የኤሌክትሮኒክስ ሰነዶችን እንዲሁም የሰው ምስክሮችን ይጨምራል፡፡
14. **"መረጃ አቅራቢ"** ማለት ተጨባጭ መረጃ ለባንኩ ወይም ለሕግ አስከባሪ አካላት የሚያቀርብ ሰው ነው፡፡
15. **"ሕገ-ወጥ ድርጊት"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ /እንደተሻሻለ/አዋጅ ቁጥር 591/2000 ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ጥሬ ብር መያዝ፣ የዉጭ ሀገር ገንዘብ ወይም ወርቅ በሕገ ወጥ መንገድ መያዝ ወይም ማዘዋወር፣ ሀሰተኛ የገንዝብ ኖት ማተም፣

መያዝ ወይም ማዘዋወር፡ ህገወጥ በሆነ የገንዘብ ማስተላለፍ ሀዋላ ስራ የመሰማራት ድርጊት ነዉ፡፡

16. “ብር” ማለት የኢትዮጵያ ሕጋዊ ገንዘብ ኖት ነዉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ/እንደሻሻለ/አዋጅ ቁጥር 591/2000 ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ የሚፈጸም ሕገ ወጥ ድርጊትን በተመለከተ የሚቀርብ መረጃ አቀራረብ፣ አያያዝ፣ የተያዙ ሕገ ወጥ ዕቃዎች ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ስለሚሆኑበት ሁኔታ እና ወሮታ አከፋፈል የተመለከቱ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መረጃ ስለመስጠት

4. <u>መሠረቱ</u>

በአገሪቱ በየትኛውም ሥፍራ ሕገ-ወጥ ድርጊት መኖሩን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤት ወይም ሕግ አስከባሪ አካል ወይም ለብሔራዊ ባንክ ዋናዉ መሥሪያ ቤት ወይም በአቅራቢያዉ በሚገኝ የብሔራዊ ባንክ ቅርንጫፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

5. <u>ጥቆማዎችና መረጃዎች እንደ መረጃ የማይቆጠሩባቸዉ አግባቦች</u>

5.1 ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የሚከተሉት ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ መረጃዎች ወይም ጥቆማዎች እንደ መረጃ አይቆጠሩም፡-

ሀ/ ቀደም ሲል በሌላ ጠቋሚ መረጃ የቀረበባቸው፣

ለ/ በአሳማኝ እና በበቂ ማስረጃ እና መረጃ ያልተደገፉ ጥቆማዎች፤

ሐ/ መረጃዉ ከመቅረቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ ወይም በሌላ የመንግስት አካል መረጃዉ የሚታወቅ ከሆነ፤

መ/ በዚህ መመሪያ መሠረት መረጃዉ ተሟልቶ ካልቀረበ፡፡

5.2 ብሔራዊ ባንክ ከጠቋሚው የቀረበለትን መረጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ

(1) መሠረት ካልተቀበለው ወዲያውኑ ለጠቋሚው በጽሑፍ ምስጥራዊነቱን በጠበቀ መልኩ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 6. <u>የጥቆማ ወይም የመረጃ አቀባበል</u>

6.1 ብሔራዊ ባንክ ወይም ሕግ አስከባሪ አካል ሕገ ወጥ ድርጊት ስለመኖሩ የቀረበለትን መረጃ ተቀብሎ እንደ መረጃ የሚቆጥረዉ፡-

ሀ/ ከጠቋሚው በስተቀር በሌላ በማናቸውም ዘዴ መረጃውን ማግኘት የማይቻል ከሆነ፣ ወይም

ለ/ በዚህ አንቀጽ በፊደል "ሀ" የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረበዉ የሕገ ወጥ ድርጊት መረጃ ቀደም ሲል በብሔራዊ ባንክ ወይም በሕግ አስከባሪ አካል የሚታወቅ ቢሆንም የቀረበው መረጃ ሕገ ወጥ ድርጊቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ ወይም ሕገ ወጥ ድርጊት ስለመፈጸሙ በበቂ ሁኔታ የሚያስረዳ ወይም ተጠያቂነትን ለማሰፈን የሚረዳ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

6.2 ጥቆማ አቅራቢዉ በአካል ወይም የጥቆማ ፎርም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ድህረ ገጽ ላይ በማዉረድ መረጃዉን ሞልቶ በኢሜል፣ፋክስ፣በፖስታ አድራሻ መላክ አለበት፡፡

## 7. <u>የመረጃ ማቅረቢያ ዘዴዎች</u>

7.1 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ላይ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ማንኛውም ጠቋሚ ለሕግ አስከባሪ አካል ወይም ለብሔራዊ ባንክ ጥቆማውን በግንባር፣ በጽሑፍ፣ በቃል በስልክ፣ በፋክስ፣ በፖስታ፣በኢ-ሜይል ወይም በሌሎች ማናቸውም ዘዴዎች ሊያቀርብ ይችላል፡፡

7.2 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአካል በመቅረብ ጥቆማ የሚቀርብበትን አግባብ እና ሂደት የተመለከተ መረጃ የሚሰጥበት ስልክ ቁጥር ለህዝቡ ይፋ በማድረግ በዚሁ አግባብ ጥቆማ እና መረጃ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

7.3 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጥቆማ የሚቀርብበትን እና በቀጣይ የሚፈጽሙ የስራ ክንውኖችን የተመለከተ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## 8. የጥቆማ አመዘጋገብ

8.1 ማንኛውም መረጃ በመረጃ መቀበያ ቅጽ ላይ እንደቅደም ተከተሉ በጥንቃቄ ይሞላል፤ መረጃውን ላቀረበው ሰውም መረጃውን ስለማቅረቡ የሚያረጋግጥ ሰነድ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

8.2 ለሕግ አስከባሪ የቀረበ መረጃ በ48 ሰዓት ውስጥ ባሉት የመገናኛ ዘዴዎች ለብሔራዊ ባንክ ይላካል፣ በንዑስ አንቀጽ(1) በተመለከተው መሠረትም ይመዘገባል፡፡

## 9. የመረጃ ምስጢራዊነት

9.1 በሕገ-ወጥ ድርጊት ላይ ከሚሰጥ ማንኛውም ጥቆማ እና መረጃ ጋር በተያያዘ የመረጃ ሰጪዉን ማንነት አግባብነት ካለዉ የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ወይም አግባብነት ካለዉ የሕግ አስከባሪ አካል በስተቀር ከማንም ሰው ወይም አካል ምስጢራዊ ሆኖ ይጠበቃል፡፡

9.2 ብሔራዊ ባንክ የመረጃ ሰጪውን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ማናቸውም የመረጃ ብክነት እንዳይኖር ከፍተኛ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

9.3 ማንኛውም የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ የተቀበለውን ጥቆማ በሕግ ከተፈቀደለት አካል ውጪ መረጃውን በጽሁፍ ፣ በቃል ወይም በሌላ በማናቸውም ዘዴ ሆን ብሎ ለማንኛውም ሰው አሳልፎ የሰጠ ወይም ምስጢራዊነቱን ያባከነ እንደሆነ በወንጀል ሕግ መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በዲሲፕሊን ተጠያቂ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 10. የመረጃ ሰጪ የምስጢር መለያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውንም ጠቋሚ የሚለይበት እንዲሁም ከጠቋሚው ጋር ለሚኖረው ማንኛውም ግንኙነት የተለየ የሚስጢር መለያ ቁጥር ለእያንዳንዱ ጠቋሚ ይሰጣል፡፡

## 11. ስለመረጃ ቅጽ፣ ይዘት፣ አቀማመጥ እና ስርጭት

በዚህ መመሪያ መሠረት ሕገወጥ ድርጊት መፈጸምን በተመለከተ የሚቀርቡ የጥቆማ መረጃዎች መቀበያ እና መከታተያ ማኅደሮች፣ ቅጾች፣ የቅጾችን ይዘት ዝርዝርና ብዛት፣

አያያዝ እና አጠባበቅ እንዲሁም የመረጃ አያያዝ በተመለከተ ብሄራዊ ባንክ በሚያወጣዉ የአሰራር ማንዋል መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈጸመበት ጥሬ ብር፣ የዉጭ ሀገር ገንዘብና ወርቅ አያያዝ

### 12. የተያዙ ንብረቶች አቀማመጥ

12.1 ሕገወጥ ድርጊቱ የተፈጸመዉ በጥሬ ብር ወይም በዉጭ ሀገር ገንዘብ ላይ ከሆነ የሕግ አስከባሪ አካል እንዲሁም የብሔራዊ ባንክ የውስጥ ኦዲተር ባለበት ገንዘቡ ተቆጥሮና ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ገቢ ተደርጎ ለዚህ መመሪያ ማስፈጸሚያ በተከፈተዉ የባንክ ሒሳብ እንዲመዘገብ ይደረጋል ፡፡

12.2 ሕገ ወጥ ድርጊቱ የተፈጸመው ወርቅ ላይ ከሆነ የሕግ አስከባሪዉ አካል ወርቁን በመያዝ ወዲያውኑ የባንኩ የዉስጥ ኦዲተር ባለበት የወርቁ ትክክለኛነት ተረጋግጦ ለብሔራዊ ባንክ ዋና መስሪያ ቤት ወይም በአቅራቢያ ባለ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቅርንጫፍ ገቢ ያደርጋል፡፡

### 13. በተያዘ ዕቃ ላይ እንዳይፈጸም የተከለከለ ተግባር

13.1 ማንኛውም የባንኩ ሠራተኛ ወይም ሕግ አስከባሪ የተያዘን ወይም በቁጥጥር ሥር የዋለን ጥሬ ብር፣ የዉጭ ሀገር ገንዘብ፡ ሀሰተኛ የገንዝብ ኖት ፡ ወይም ወርቅ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲውል ማድረግ፣ መሸጥ፣ መለወጥ፣ ማውደም፣ መቀነስ፣ እሽጉ እንዲፈታ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ፣ ለአያያዝ እና ለአቀማመጥ እንዳይመች ማድረግ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ሕገ ወጥ ተግባራትን መፈጸም የለበትም፡፡

13.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘረውን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ የተገኘ የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ወይም ሕግ አስከባሪ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

# የወሮታ ክፍያ እና አፈፃፀም

## 14. መሠረቱ

14.1 ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ለሕግ አስከባሪ በሚቀርብ ጥቆማ ወይም መረጃ ሕገ-ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን የጥሬ ብር፣ ሀሰተኛ የገንዝብ ኖት፣ ሀሰተኛ የገንዝብ ኖት ማተሚያ መሳሪያዎች፣ ወርቅ ወይም የዉጭ ሀገር ገንዘብ ከተያዘ እንዲሁም ህገ ወጥ ድርጊት ፈጻሚዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ ከተደረገ ጠቋሚው በዚህ መመሪያ መሠረት የወሮታ ክፍያ ይከፈለዋል፡፡

14.2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተቀመጠዉ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሠረት የወሮታ ክፍያ የሚከፈለው ለብሔራዊ ባንክ ገቢ የሆነው ሕገ-ወጥ ድርጊት የተፈጸመበት ዕቃ በሽያጭ ወይም በሌላ በማንኛወም መንገድ ለብሔራዊ ባንክ እንዲተላለፍ ከተደረገ በኋላ እና ሕጋዊ ዉሳኔ ሲያገኝ ነዉ፡፡

14.3 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8.1 መሠረት የጠቋሚነት ማስረጃ የተሰጠው ሰው የክፍያ ጥያቄ በሚያቀርብበት ወቅት የማስረጃውን ዋና ቅጂ ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

14.4 የተወረሰዉ ዕቃ ጥሬ ብር ከሆነ የወሮታ ክፍያ ተቀንሶ በመንግስት ሒሳብ ገቢ ይደረጋል፡፡

14.5 የተወረሰዉ ዕቃ የዉጭ ሀገር ገንዘብ ወይም ወርቅ ከሆነ ከሽያጩ የወሮታ ክፍያ ተቀንሶ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ይደረጋል፡፡

## 15. ሕገ-ወጥ ዕቃ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ሆኗል ስለሚባልበት ሁኔታ

ህገ ወጥ ዕቃ ለብሄራዊ ባንክ ገቢ ሆኗል የሚባለው በሕገ-ወጥ ዕቃ ባለቤት፣ በግብረ አበሮቹ እና/ወይም በተባባሪዎቹ ላይ ባሉበትም ሆነ በሌሉበት በቀረበባቸው የወንጀል ክስ መሠረት ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት በዕቃው ላይ የውርስ ወይም ተዛማጅ ውሳኔ ሲሰጥ ወይም ተከሳሹ ፍርድ ቤት ባለመቅረቡ ምክንያት ክስ የማቅረብ መብት ተጠብቆ በተዘጋ ክስ ላይ ፍርድ ቤት ሕገ- ወጥ ዕቃ ተሽጦ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ እንዲሆን ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው፡፡

## 16. የወሮታ ክፍያ መጠን

16.1 በሕገ ወጥ ድርጊት ምክንያት የተያዘዉ ጥሬ ብር ፣ የዉጭ ሀገር ገንዘብ ወይም ወርቅ ከሆነ ለጠቋሚው የሚከፍለው ክፍያ አሰራ አምስት በመቶ (15%) ይሆናል፡፡

16.2 በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16.1 ላይ የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕገ ወጥ ድርጊት ምክንያት የተያዘዉ የዉጭ ሀገር ገንዘብ ከሆነ ብሔራዊ ባንክ ለጠቋሚው የውጭ ሀገር ገንዘብ ተወርሶ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ እንዲደረግ በተወሰነበት እለት ባለዉ የዉጭ ምንዛሪ መግዣ ዋጋ ስሌት መሰረት የወሮታ ክፍያዉን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16.1 መሠረት ይፈጽማል፡፡

16.3 በዚህ አንቀጽ ንዕሱ አንቀጽ 16.1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሕገ ወጥ ድርጊት ምክንያት የተያዘዉ ወርቅ ከሆነ ብሔራዊ ባንክ ለጠቋሚ ወርቁ ተወርሶ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ እንዲደረግ በተወሰነበት እለት ባለዉ አለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ስሌት መሰረት የወሮታ ክፍያዉን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16.1 በተመለከተዉ መሠረት ይፈጽማል፡፡

16.4 በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀርብ ጥቆማ በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች በጋራ ከቀረበ በጋራ ይመዘገባሉ፣ የሚከፈለው የወሮታ ክፍያም በጋራ ይፈጸምላቸዋል፣ ሆኖም በተናጠል ከቀረቡ እንደየድርሻቸው ክፍያ ይፈጸማል፡፡

16.5 ሕገ ወጥ ድርጊቱ የተፈጸመዉ ከሀሰተኛ ገንዘብ ኖት ጋር በተያያዘ ከሆነ የወሮታ ክፍያ መጠን ከዚህ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡

I. የተያዘው ሀሰተኛ ገንዘብ ከብር አስር ሺህ (10,000) እስከ ብር መቶ ሺህ (100,000) ከሆነ ብር ሀያ ሺህ (20,000) ይከፈላል፡፡

II. የተያዘው ሀሰተኛ ገንዘብ ከብር መቶ ሺህ (100,000) እስከ አንድ ሚሊዮን (1,000,000) ከሆነ ብር ሀምሳ ሺህ (50,000) ይከፈላል፡፡

III. የተያዘው ሐሰተኛ ገንዘብ ከብር አንድ ሚሊዮን (1,000,000) እስከ ብር አስር ሚሊዮን (10,000,000) ከሆነ ብር መቶ ሺህ (100,000) ይከፈላል፡፡

IV. የተያዘው ሐሰተኛ ገንዘብ ከብር አስር ሚሊዮን (10,000,000) በላይ ከሆነ ብር ሁለት መቶ ሺህ ይከፈላል፡፡

16.6 በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16.5 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሀሰተኛ የገንዘብ ኖት የሚታተምባቸውን ቦታዎች እና ተያያዥ መሳሪዎች በተመለከተ ጥቆማ በማቅረብ የድርጊቱ ፈጻሚዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ ላስቻለ ጠቋሚ ብር ሁለት መቶ ሺህ (200,000) የወሮታ ክፍያ ይከፈላል፡፡

16.7 ህገወጥ የገንዘብ ማስተላለፍ ሀዋላ ድርጊት ላይ የሚሳተፉ ሰዎችን የተመለከተ መረጃ በማቅረብ እነዚህ አካላት በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያስቻለ ጠቋሚ የብር ሃያ አምስት ሺህ ብር (25,000) የወሮታ ክፍያ ይከፈላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. <u>የይርጋ ጊዜ</u>

17.1 የወሮታ ክፍያው መፈጸም ካለበት ጊዜ ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ የክፍያ ጥያቄ ካልቀረበ መብቱ በይርጋ ይታገዳል፡፡

17.2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የክፍያ ጥያቄው የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለመሆኑ አሳማኝ ማስረጃ ከቀረበለት ብሔራዊ ባንክ የጊዜ ገደቡን ለተጨማሪ 6 ወራት ሊያራዝም ይችላል፡፡

18. <u>መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ መስከረም 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**<u>አዲስ አበባ መስከረም 26 ቀን 2015 ዓ.ም</u>**

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

## የጥቆማ መረጃ መቀበያ ፎርም ቁጥር

### በመረጃ አቅራቢ የሚሞላ

| የሚስጥር ኮድ | መረጃው የቀረበበት ቀን __. | የመረጃ ቁጥር |
|---|---|---|
| | | |

1. የመረጃ አቅራቢው ስም ----
2. የትውልድ ዘመን ቀን ---- ወር ---- ዓ.ም ----
3. የመረጃ አቅራቢው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር-----------
4. የመረጃ አቅራቢው አድራሻ፡ ስልክ ---- ፖስታ ሳጥን ቁጥር ----
   ክልል/ከተማ አስተዳደር ------------------ ክ/ከተማ--------------- ወረዳ--------------- ልዩ ቦታ-----------
5. መረጃውን የተቀበለው ሰራተኛ ስም እና የስራ መደብ----------------------------------
6. መረጃ የቀረበበት ግለሰብ/ድርጅት ስም-----------------------------------------------
7. መረጃ የቀረበበት ግለሰብ/ድርጅት አድራሻ-----------------------------------------
8. መረጃ አቅራቢው መረጃ ከቀረበበት ግለሰብ/ድርጅት ጋር ያለው ወይም የነበረው ግንኙነት-----------------------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------
9. በሕገ ወጥ ድርጊት ተካፍለዋል ብሎ የሚጠረጥራቸው ሰዎች ብዛት ግምት -------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
10. መረጃ አቅራቢው ከሚሰጠው መረጃ ጋር በተያያዘ ያቀረባቸው ማስረጃዎች
    1. ---------------------------------------------------------------------------------------------
    2. ---------------------------------------------------------------------------------------------
    3. ---------------------------------------------------------------------------------------------
11. የሚሰጠውን መረጃ አጠቃላይ ዝርዝር ሁኔታ/ ድርጊቱ የተፈጸመበትን መንገድ

    ------------------------------------------------------------------------------------------------
    ------------------------------------------------------------------------------------------------
12. እኔ ስምና አድራሻዬ ከዚህ በላይ የተመለከተው በዚህ ፎርም ላይ የተመለከተውን መረጃ በገዛ ፈቃደኝነት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአካል ቀርቤ መስጠቴን አረጋግጣለሁ፡፡
13. እኔ እስከማውቀው ድረስ ያቀረብኩት መረጃ ትክክለኛ እና ተአማኒ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡
14. ፊርማ ______________